# ደንብ

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

**ተዛማጅ ግብአቶች፦** EBH-RA፣ EBI-RA፣ EEA፣ EEB-RA፣ IGN፣ IPD-RA፣ JED፣ JEE፣ JEE-RA፣ JFA-RA፣ JHC፣ JHC-RA፣ KLA፣ KLA-RA

**ሃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፦** ዋና የሥራ ኃላፊ
Chief of School Support and Improvement የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻል ዋና ኃላፊ

## የተማሪ ትራንስፖርት

I. **ዓላማ**

የዚህ ደንብ ዓላማ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪዎች መጓጓዣ አገልግሎት ህጉ በሚፈቅደው መሠረት እንዲሆን እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎች ወደ ትምህርት እና ከትምህርት ቤት መልስ በሚሰጣቸው መጓጓዣ የእንቅስቃሴ ደህንነት ኃላፊነቶችን ለመግለጽ ነዉ።

II. **ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች**

በዋና የሥራ ኃላፊው ሥር፣ የትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት ዳይረክተር (DOT)፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አውቶቡሶች ለተማሪ መጓጓዣ እና ደህንነቱ የተጠበቀና የተቀላጠፈ አሰራር ኃላፊነት አለበ(ባ)ት። ስለ እግረኛ ተማሪዎች ደህንነት እና ቁጥጥር DOT ከሚመለከታቸው የፖሊስ እና ሌሎች ህዝባዊ ኃላፊነት ካላቸው ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያደርጋል። የትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት ዳይረክተር (DOT)፣ ከትምህርት ቤት ርእሰመምህራን ጋር በመሆን ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት መልስ የተማሪዎችን ጉዞ በሚመለከት ደህንነቱ የተጠበቀ እና ቀልጣፋ እንዲሆን የሚደረጉትን ውሳኔዎች ያስተባብራል/ታስተባብራለች።

A. *መጓጓዣ የሚቀርብባቸው እና የማይቀርብባቸው አካባቢዎች*

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶችን የሚያካልሉ የመጓጓዣ አካባቢዎች በትምህርት ቦርድ አማካይነት እንደሚከተለው ተወስኗል፦

የኤለመንተሪ ትምህርት ቤቶች—ከ 1 ማይል በላይ፣
የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች—ከ1.5 ማይሎች በላይ፣
የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች—ከ2 ማይሎች በላይ።

እርቀቱ የሚለካው ከቅርቡ የመኖሪያ ቤት መነሻ ፊትለፊት እስከ አቅራቢያ ትምህርት ቤት በር መታጠፊያ ይሆናል።

1. ቦርድ በደነገገው ርቀት ላይ ለሚኖሩ ተማሪዎች ተገቢ የሆነ በእግር የሚያስኬድ መስመር አለመኖሩን የ DOT ከወሰነ፣ ለተማሪዎች የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣል።

2. መጓጓዣ የሚመደብበት እና የማይመደብበት አካባቢ መስመር በሚከለልበት ወቅት፣ የቤቶች አቀማመጥ፣ የመንገድ መጋጠሚያዎች፣ ዋና/አውራ መንገዶች፣ ጅረቶች፣ ፓርኮች፣ የእግር ጉዞ የሚፈቀድባቸው ቦታዎች፣ የንግድ ንብረቶችን፣ ባዶ ቦታ፣ ያልተለመዱ ወጣገብ ቦታዎች፣ እና

ሌሎች የመሣሠሉ ገፅታዎች ጋር እንዲገጣጠም፣ እነዚህን እርቀቶች የ DOT ዳይሬክተር በአንድ አስረኛ ማይል ለማስረዘም ይችላል/ትችላለች።

B. የመጓጓዣ አገልግሎት ደረጃዎች

ቦርድ በሚወስናቸው የመጓጓዣ አካባቢዎች ነዋሪዎች የሆኑ ተማሪዎች ወይም በፌደራል ህግ መስፈርት መሠረት ብቁ የሆኑ ተማሪዎች እንደሚከተለው የመጓጓዣ አገልግሎት ለማግኘት ይችላሉ፡-

1. አጎራባች የአውቶቡስ አገልግሎት፣ ከአካባቢ/ጎረቤት የአውቶቡስ ማቆሚያዎች ወደትምህርት ቤት ማጓጓዣ ተብሎ የተገለጸው፣ በአካባቢ ትምህርት ቤት አቅራቢያ ለሚኖሩ ወይም ለሚከታተሉበት ትምህርት ቤት ምድብ/ኮንሰርሽያ አቅራቢያ ለሚኖሩ ተማሪዎች መጓጓዣ ይሰጣል።

2. የተማከለ የአውቶቡስ አገልግሎት፣ ከአማካይ ቦታ መጓጓዣ ተብሎ እንደተገለጸው ለምሣሌ፡- ከአጎራባች የኤለመንተሪ ትምህርት ቤት፣ እስከ ፕሮግራሙ ቦታ ድረስ፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) Options (Guide to Countywide Programs)booklet, in accordance with Board action, attendance areas, transportation services, and funding levels ላይ እንደተገለጸው በተለያዩ አይነት ፕሮግራሞች ላይ ለሚሣተፉ ተማሪዎች ይሰጣል። ተገቢ የሆነ የእግር ጉዞ መንገድ ቢኖርም ባይኖርም ተማሪዎችን እስከ አማካይ የአውቶቡስ ማቆሚያዎች ለማጓጓዝ እና ከዚያ ለመውሰድ ወላጆች/ሞግዚቶች ኃላፊነት አለባቸው።

3. ከሚማሩበት ትምህርት ቤት የአውቶቡስ ማጓጓዣ ከተመደቡት መስመር አካባቢዎች ውጪ የሚኖሩ ተማሪዎች አገልግሎት ለመስጠት የሚቻለው ቦታ መኖሩን መሠረት በማድረግ ነው። ወላጆች/ሞግዚቶች በአካባቢ ወይም በማእከላዊነት ወደተወሰነው የመነሻ/የመድረሻ የመጓጓዣ አካባቢ ተማሪዎችን የማድረስም ሆነ የመመለስ ኃላፊነት አለባቸው። የተማሪ ደህንነት አደጋ ላይ በሚሆንበት ወቅት ክልከላ/ገደብ ይደረጋል።

4. ስለ ብቁነት የፌደራል ህጎችን ለሚያሟሉ ተማሪዎች የተሻሻሉ ደረጃዎች የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣል።

   a) የአካል ስንኩልነት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ድንጋጌ/Individuals with Disabilities Education Act (IDEA)

      የአካል ስንክልና ላለባቸው ተማሪዎች የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም ላይ /Individualized Education Program (IEP) በተገለጸው መሠረት መጓጓዣ የሚሰጠው የፕሮግራሙ አካል ተደርጎ ነው።

   b) ሰክሽን 504 የመልሶ ማቋቋም ድንጋጌ/Section 504 of the Rehabilitation Act

      የአካል ስንክልና ያለባቸውን ተማሪዎች "ሰክሽን/Section 504" ላይ በተገለጸው መሠረት ለማስተናገድ/እንደ አኮመዴሽን መጓጓዣ ይሰጣል።

   c) ማኬኒ-ቨንቶ የቤት አልባነት እርዳታ ድንጋጌ/McKinney-Vento Homeless Assistance Act

      ቤት አልባ ለሆኑ ተማሪዎች የመጓጓዣ አገልግሎት የሚሰጠው በተገለጸው መሠረት ይሆናልMcKinney-Vento Homeless Assistance Act of 1987፣ በተሻሻለው መሠረትEvery Student Succeeds Act of 2015።

5. የልዩ ትምህርት የመጓጓዣ አውቶቡሶች በሚሰጡት አገልግሎት በተመሣሣይ/በዚያው ትምህርት ቤት ለሚማሩ የልዩ ትምህርት ተማሪ ወንድም/እህት ጭምር አገልግሎት ይሰጣሉ። ልዩ ትምህርት ለሚከታተለው/ለምትከታተለው ተማሪ የመጓጓዣ አገልግሎት በሚያበቃበት ጊዜ ለወንድም-ለእህትም የመጓጓዣ አገልግሎቱ ያበቃል።

C. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ያልሆኑ/Non-MCPS የመጓጓዣ አገልግሎቶች

በ "Section II.B.4" ላይ በተገለጸው መሠረት ለተሻሻለ የመጓጓዣ አገልግሎት ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች አገልግሎት ለመስጠት በተቻለ መጠን የ DOT ሠራተኞች የ MCPS-ንብረት የሆኑ ተሽከርካሪዎችን ይገለገላሉ። ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች በ MCPS-ንብረት ተሽከርካሪዎች የተመቻቸ የመጓጓዣ አገልግሎት ለመስጠት ካልተቻለ የ DOT ዳይሬክተር የንግድ ተሽከርካሪዎችን ለመጠቀም ይሞክራል/ትሞክራለች እና/ወይም የተማሪው(ዋ)ን ፍላጎት የሚያሟላ በጣም የተመጠነ የትራንስፖርት ወጪ በቀጥታ ለወላጆች/ለሞግዚቶች ወይም ለሌሎች ግለሰቦች መልሶ የመክፈል እርምጃ ይወስዳል/ትወስዳለች።

1. የንግድ መጓጓዣ አገልግሎቱ በማቴሪያል ማኔጅመንት ዲፖርትመንት የንብረት ግዢ ዳይሬክተር አማካይነት ድርድር ከተደረገ በኋላ በ DOT ዳይሬክተር በቅድሚያ ፈቃድ መሰጠት አለበት። እንደዚህ አይነት ኮንትራቶች ከ COMAR ጋር የተገናኙ የተማሪ መጓጓዣ መስፈርት (13A.06.07) እና MCPS DOT መመሪያዎችን ማሟላት አለባቸው። በማናቸውም ጊዜ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተሽከርካሪ የሚመቻች ከሆነ፣ የንግድ አገልግሎቱ ይቋረጣል።

2. ወላጆች/ሞግዚቶች ተመላሽ እንደሚደረግላቸው የሚጠብቁት የመጓጓዣ እና ተዛማጅ ወጪዎች በ DOT ዳይሬክተር አማካይነት በቅድሚያ ፈቃድ መሰጠት አለበት። የተመላሽ መጠን ለሠራተኞች መጓጓዣ፣ ቦርድ ካፀደቀው የማይሌጅ መጠን ሊያልፍ አይችልም። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተሽከርካሪዎች ዘግይቶ የሚስተካከል ከሆነ፣ ተጨማሪ ወጪዎች አይፀድቁም።

D. የተማሪ ደህንነት

1. የ DOT ዳይሬክተር ወይም ተወካይ አውቶቡሶችን ጉድለት እንደሌለባቸው እና የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ፣ የአውቶቡስ ማቆሚያዎችን፣ የተፈቀዱ የእግረኛ መንገዶችን፣ እና ለትምህርት ቤት የትራፊክ ቁጥጥር ይዞቶችን ይገመግማል/ትገመግማለች።

   a) የተማሪዎችን ደህንነት ለመጨመር የ MCPS አውቶቡሶች ካሜራዎች ተገጥሞላቸዋል። ካሜራዎቹ በአውቶቢሱ ውስጥ እና በውጭ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ሪኮርድ ያደርጋሉ።

      (1) ለትምህርት ቤት አውቶቡሶች ካሜራዎችን የማጠናከር ፕሮግራም አማካይነት፣ የ MCPS DOT አጋሮች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የፖሊስ ዲፓርትመንት፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ የመንግስት አስተዳደር፣ የትምህርት ቤት አውቶቡስን ጥሶ የማለፍ ህጎች ለህዝብ ይፋ ተደርገዋል እና የትምህርት ቤት አውቶቡሶችን ህግ ለተላለፉ አሽከርካሪዎች በ MCPS የትምህርት ቤት አውቶቡሶች ላይ በተገጠሙ ካሜራዎች የተገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የህግ ጥሰት ወረቀቶች/ቲኬቶች ተሰጥተዋል።

(2) የ DOT ባልደረባዎች የአውቶቡስ ውስጥ በአብዛኛው በቃል የማይናገሩ ተማሪዎች በሚጓዙባቸው አውቶቡሶች ላይ የተገጠሙትን የካሜራ ቀረጻዎችን ይገመግማሉ።

b) የ MCPS DOT ልዩ እንክብካቤ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለሚያጓጉዙ አውቶቡሶች የደህንነት ጥበቃ ፕሮቶኮሎችን/መመሪያዎችን ከማዘጋጀቱም በላይ ለአውቶቡስ አሽከርካሪዎች እና ለአቴንዳንቶች መደበኛ ስልጠና ይሰጣል። የደህንነት መመሪያዎች/ፕሮቶኮሎች ለ MCPS አሽከርካሪዎች እና ለአቴንዳንቶች ከወላጆች/ሞግዚቶች፣ ከመምህራን፣ እና/ወይም ፓራኢጁኬተሮች ጋር ልዩ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ፍላጎት ስለማሟላት እቅድ ስለማድረግ የሚገናኙበትን መመሪያ ይሰጣል።

c) ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት መልስ ስለተማሪ የመጓጓዝ-ጥያቄዎች አስቸጋሪ ሁኔታ መኖር-አለመኖሩን በመመርመር ዋስትና ያለው እርምጃ እንዲወስድ/እንድትወስድ ወደ DOT ክለስተር ሱፐርቫይዘር ይመራሉ።

2. በእግር መራመድን የሚጠይቁ መስመሮች

a) በእግር የሚራመዱበት መስመር የሚወሰነዉ/የሚመደበዉ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፦

(1) በድረ-ገጽ ላይ የሚገኝ የጎረቤት አካባቢን የመንገድ ገጽታ የሚያሳይ መልክአምድራዊ አቀማመጦች-ቅርጾች

(2) ስለ ተማሪ ደህንነት ስልጠና በተሰጣቸው የ DOT ሥራ ባልደረቦች የመስክ ጉብኝቶች

(3) በሌሎች አጎራባች ቦታዎች ተነጻጻሪ የሆኑ በእግር የሚያስኬዱ መስመሮችን ማወዳደር/መገምገም

(4) አሁን ያሉት የደህንነት ገጽታዎች እና ደህንነትን የሚያደናቅፉ ነገሮች

(5) በእግር መተላለፊያ አካባቢዎች የእግረኛ/የባለተሽከርካሪ አጠቃቀምን መመልከት

b) ተገቢ የሚሆነው በእግር የሚያስኬድ እርቀት በ Board Policy EEA በተገለጸው መሠረት የተማሪ መጓጓዣ/Student Transportation፣ነገር ግን በጣም አቋራጭ የሆነ ወይም በጣም ቀጥታ የሆነውን አይከተልም።

c) በጊዜያዊ ሁኔታዎች ለምሳሌ፦ ዝናብ ከዘነበ በኋላ የረጋ ውኃ፣ በረዶ እና/ወይም በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ወቅት የሚያንሸራትት በረዶ መንገድ ዳር በመከመሩ ምክንያት በመሣሉት የ DOT አገልግሎት ለውጥ አይደረግም።

3. አቋራጭ መንገዶች እና አዋቂ/ጎልማሳ አሻጋሪ ጋርዶች

በእግር ማቋረጫ አካባቢዎች ወይም እና አዋቂ የመንገድ ማቋረጫ ጥበቃዎችን በሚመለከት በ DOT ዳረክተር፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ ዲፓርትመንት የትምህርት ቤት ደህንነት ክፍል፣ እና ከሞንትጎመሪ ካውንቲ DOT ጋር በጋራ ይወሰናል። የአዋቂ/ጎልማሳ የመንገድ ማቋረጫ

ጥበቃዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ የፖሊስ ዲፓርትመንት አማካይነት ተቀጥረው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በሚያቀርበዉ ጥያቄ መሠረት ይመደባሉ።

4. የአውቶቡስ መስመሮች/Bus Routes

አውቶቡሶች የሚሠማሩት ደህንነትን እና ብቃት/ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘት በሚያስችል መንገድ ነው። DOT የትምህርት ቤት አውቶቡሶችን መስመር የመመደብ እና ተማሪዎችን ለመጫን እና ለማውረድ የመቆሚያ ስፍራዎችን የመወሰን ኃላፊነት አለበት። ከዚህ የሚከተለው ግንዛቤ ውስጥ ይገባል፦

a) አውቶቡሶች መጓዝ ያለባቸው መስመሮች መጠናቸውን እና ክብደታቸውን ለመሸከም እንደሚችሉ ዲዛይን በተደረጉ መንገዶች እና ድልድዮች ብቻ ነው።

b) የጉዞ መስመሮች የሚወሰኑት ከተማሪ መኖሪያ ቤት እስከተመደበው የአውቶቡስ መቆሚያ በቦርድ ፖሊሲ/Board Policy EEA ላይ ከተገለጸው በማይርቅ መሠረት ነውየተማሪ መጓጓዣ/Student Transportation፦

የኤለመንተሪ ትምህርት ቤቶች—1 ማይል
የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች/ሚድል ስኩልስ—1.5 ማይሎች
የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች—2 ማይሎች

c) መደበኛ የትምህርት አውቶቡሶች መስመር በመተላለፊያ መንገዶች ይሆናል። ነገር ግን፣ ከዋናው መንገድ የተለየ እንዲሆን ሁኔታዎች የሚያስገድዱ ከሆነ፣ አውቶቡሶች የመተላለፊያ መንገድ በሌላቸው መስመር (ለምሳሌ፦ አልፎ የሚኬድበት የሌላቸው መጨረሻው ዝግ የሆኑ መንገዶች፣ አደባባዮች/dead-end streets, courts, and cul-de-sacs) ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ሁኔታዎች ሊመደቡ ይችላል፦

(1) ለአውቶቡስ የመዞሪያ ቦታ ካለ።

(2) ከመተላለፊያ መንገድ በመውጣት ለመታጠፍ እና ወደመንገድ ተመልሶ ለመግባት ችግር ከሌለበት።

5. ስለተማሪ ደህንነት እና ሠላም የትምህርት ቤት እና የወላጅ ትብብር/ኢጋርነት

ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት መልስ በሁሉም የመጓጓዣ አይነት በሠላም ለመንቀሳቀስ ተማሪዎች፣ ወላጆ/ሞግዚቶች፣ የትምህርት ቤት ባልደረቦች፣ እና የ DOT ሠራተኞች መካከል ትብብር እንዲኖር የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊ ስኩልስ (MCPS) ያበረታታል።

a) የአውቶቡስ አሽከርካሪ/የአውቶቡስ አቴንዳንት

የአውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) እና አተንዳንቱ(ቷ)፣ ከተመደቡ፣ ስለ ሠላማዊ የአውቶቡስ ጉዞ ልምዶች ማበረታታት፣ የዲስፐሊን ጉዳዮችን መተግበር እና ማሳወቅን፣ እና በጤናማ ሁኔታ አውቶቡስ ስለመሣፈር እና ከአውቶቡስ ስለመውረድ የመንገር/የመምራት ኃላፊነት አለባቸው።

b) ርእሰ-መምህር/Principal

ርእሰመምህር የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉት/አላት፦

(1) ስለትምህርት ቤት አውቶቡስ ደህንነት ደንቦች፣ ሠላማዊ የእግር ጉዞ፣ እና ሠላሚዊ የሆነ አዎቶቡስ የመጠበቅ ሥርአት በትምህርት ቤት የመማሪያ ክፍል ትምህርት መስጠት

(2) በትምህርት ቤት የሚሣፈሩበትን አካባቢ ጨምሮ በቂ ቁጥጥር ይደረጋል፣ ከትምህርት ቤት አውቶቡሶች በስተቀር ተማሪዎች በሚሣፈሩበት እና በሚወርዱበት አካባቢ የሌሎች ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ በመቆጣጠር ሠላማዊ የትራፊክ ፍሰት ተፈጻሚ ይደረጋል።

c) በእግር ለሚራመዱበት አካባቢ ወይም በአውቶቡስ ማቆሚያ ስፍራ ስለተማሪዎቻቸው ሠላምና ደህንነት የወላጆች/የሞግዚቶች ኃላፊነት ነው።

(1) ወላጆች/ሞግዚቶች ለተማሪዎቻቸው እስከ አውቶቡስ ማቆሚያዎች እና ትምህርት ቤት ድረስ በእግር የሚጓዙበትን መንገድ-መስመር የመምረጥ ኃላፊነት አለባቸው።

(2) ወላጆች/ሞግዚቶች ተማሪዎቻችውን እንደየእድሜአቸው እና እንደ ብስለታቸው አግባብ በእግር በሚራመዱባቸው መንገዶች እና/ወይም በአውቶቡስ ማቆሚያ የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው። ወላጆች/ሞግዚቶች ተማሪዎቻቸው ትምህርት ቤት ወደሚያደርሳቸው አውቶቡስ እስከሚሣፈሩ እና ከትምህርት ቤት በኋላ ከአውቶቡስ ከወረዱ በኋላ ተማሪዎቻቸውን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው።

(a) ወላጆች/ሞግዚቶች በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት መልስ ከተማሪዎች ጋር እንዲራመዱ በተለይም፣ ትንንሽ ተማሪዎች፣ እና ይህንን እድል ተጠቅመው በእግር ሲጓዙ ማድረግ ስላለባቸው ጥንቃቄ፣ በሠላማዊ ሁኔታ አውቶቡስ ስለመጠበቅ፣ ስለ ትራፊክ ግንዛቤ፣ እና ለሰውነት የጤንነት እንቅስቃሴ ምሳሌ ለመሆን እንደሚጠቅም እንዲያስተምሯቸው ይበረታታሉ።

(b) ተማሪዎች አውቶቡስ ማቆሚያ ስፍራ ላይ ለአዉቶቡስ መድረሻ ከተመደበው ሰዓት አምስት ደቂያ አስቀድመው አውቶቡስ የሚቆምበት ቦታ ላይ መገኘት/መድረስ አለባቸው።

(c) ወላጆች/ሞግዚቶች የቅድመ ምዋእለ ህጻናት እና ሄድስታርት ተማሪዎችን በእኩለ-ቀን አውቶቡሶች እና የልዩ ትምህርት አውቶቡሶች በተመደበላቸው የአውቶቡስ ማቆሚያ ላይ የመቀበል ኃላፊነት አለባቸው። እነዚህን ተማሪዎች የሚቀበላቸው ከሌለ ተማሪዎቹ እና ወላጆች/ሞግዚቶች እንደገና እስከሚገናኙ ድረስ የአውቶቡስ አሽከርካሪዎቹ የተማሪዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ ያለውን መመሪያ ይከተላሉ።

(d) በዚህ አይነት አውቶቡስ ለመድረስ ወላጆች/ሞግዚቶች በማይችሉበት ጊዜ ወይም ሲረፍድባቸው፣ ልጆች ዝግጁ ይሆናሉ፣ ከዚህ በላይ (c) ላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች በስተቀር የአውቶቡስ አሽከርካሪዎች እያንዳንዱን ተማሪ ወላጅ/ሞግዚት ይቀበለው/ይቀበላት እንደሆን ለማወቅ ስለማይችሉ

ወላጆች/ሞግዚቶች በሌሉበት ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚኖርባቸው ለልጆቻቸው ማስልጠን እንዳለባቸው ይበረታታሉ።

d) የትምህርት ቤት አውቶቡስ ወይም የተማሪ አክቲቪቲ አውቶቡስ የተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ ሲስተም እንዲያስር/እንድታስር ሲያስፈልግ (ማለትም፡- በትከሻ የሚጠልቁ ቀበቶዎች)፣ ሁሉም ተሳፋሪዎች ይህንኑ በመከተል ሠላማዊ/ጤነኛ ጉዞ ማድረግ አለባቸው።

(1) ለሁሉም ተሳፋሪዎች እንደየእድሜአቸው ሁኔታ፣ በተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ በአግባቡ እንዲጠቀም/እንድትጠቀም መመሪያ ይሰጣል።

(2) በተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ የማይጠቀሙ ወይም ያለአግባቡ የሚጠቀሙ ተማሪዎች የዲስፕሊን ቅጣት ይጠብቃቸዋል።

(3) የአካል ስንክልና ያለበ(ባ)ት ተማሪ በተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ ለመጠቀም ካልቻለ/ች ወይም በአግባብ ካልተጠቀመ(ች)፣ የአውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) ለርእሰመምህር ያሳውቃል/ታሳውቃለች። ርእሰመምህሩ(ሯ) ስለ ተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ አጠቃቀም የ IEP ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልግ እንደሆነ ለመወሰን የ IEP ስብሰባ ማድረግ ያስፈልግ እንደሆነ ይወስናል/ትወስናለች።

6. በአውቶቡስ የመጓዝ መብትን መነፈግ

a) የስነምግባር እና የሠላም-ደህንነት ጥሰት የሚያደርጉ ተማሪዎች በርእሰመምህር አማካይነት ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ቅደምተከተሎች በመከተል በአውቶቡስ የመጓጓዝ ጥቅማቸው በጊዜያዊነት ሊታገዱ ወይም በቋሚነት ሊከለከሉ ይችላሉ።

(1) የአውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) MCPS Form 555-3 በመሙላት የዲስፕሊን ችግሩን በሚመለከት ተማሪው(ዋ) የፈጸማቸውን/የፈጸመቻቸውን በመዘርዘር ለርእሰመምህር ያሳውቃል/ታሳውቃለች፣የትምህርት ቤት አውቶቡስ የዲስፕሊን ሪፖርት/School Bus Disciplinary Report። በትምህርት ቤት በተወሰደው እርምጃ የዲስፕሊን ችግሩ ካልተፈታ፣ አሽከርካሪው ለ DOT ክለስተር ሱፐርቫይዘር ያስተላልፋል/ታስተላልፋለች።

(2) ርእሰመምህሩ(ሯ) ተማሪው(ዋ)ን የአውቶቡስ አገልግሎቱ ሊቋረጥበ(ባ)ት እንደሚቻል በመግለጽ ያስጠነቅቃል/ታስጠነቅቃለች እና ተማሪው(ዋ) እና ወላጆች/ሞግዚቶች በአውቶቡስ ስለመጓዝ ኮንትራት እንዲፈርሙ ያደርጋል/ታደርጋለች። የዲስፕሊን ችግሮቹ የሚቀጥሉ ከሆነ፣ ርእሰመምህሩ(ሯ) የአውቶቡስ አገልግሎት ከመቋረጡ አስቀድሞ ከወላጅ/ሞግዚት እና ከተማሪው ጋር ስብሰባ ያደርጋል/ታደርጋለች፣ ወይም እንደስነምግባሩ ባህርይ እና ውስብስብነት፣ የአውቶቡስ አገልግሎቱ በአስቸኳይ ይቋረጣል።

(3) ርእሰመምህሩ(ሯ) በተማሪው(ዋ) ላይ የቀረቡትን ቅሬታዎች እና የአውቶቡስ አገልግሎት እንዲቋረጥ መደረጉን ግልባጭ ለአውቶቡስ አሽከርካሪ፣ DOT፣ እና በሱፐርኢንተንደንቱ ጽ/ቤት ለሚመለከተው የትምህርት ዳይሬክተር፣

ስኬት፣ እና አስተዳደር በማድረግ ለወላጅ/ሞግዚት በጽሑፍ ይገልጻል/ትገልጻለች።

b) ከተማሪው(ዋ) እና/ወይም ወላጅ/ሞግዚት ጋር ኮንፈረንስ ከተደረገ በኋላ የ DOT ክለስተር ሱፐርቫይዘር በማማከር የተማሪው(ዋ) የአውቶቡስ አገልግሎት በድጋሚ እንዲቀጥል ማድረግ ይቻላል። የአውቶቡስ አገልግሎት እንደገና እንዲቀጥል መደረጉን ርእሰመምህሩ(ሯ) ለአውቶቡስ አሽከርካሪ፣ እና ለ DOT ክለስተር በጽሑፍ ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

E. አደጋ በሚፈጠርበት ወቅት ያሉ ኃላፊነቶች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች

1. አደጋዎች ሲደርሱ ተማሪዎች/ሠራተኞች በትክክል እንክብካቤ መደረግ እንዳለበት፣ ተጨማሪ ጉዳትን ስለመከላከል፣ በተቻለ ፍጥነት ተማሪዎች ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር እንዲገናኙ ማድረግ፣ እና አግባብነት ያላቸው የሚመለከታቸው ሁሉ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ እንዲደርሳቸው መደረግ እንዳለበት መመሪያዎችን እና ቅደምተከተሎችን ስለመጠበቅ DOT ስልጠና ይሰጣል። አደጋ የተፈጠረበት ቦታ ኃላፊነቶች፣ ማሳወቅ፣ እና ሪፖርት የማድረግ አስፈላጊነት ከስቴት እና የፌደራል መስፈርቶች ጋር የሚጣጣም ይሆናል።

2. አደጋ የተከሰተበት ቦታ ኃላፊነት የሚከተሉትን ያካትታል፦

a) የስምሪት ኃላፊ፣ ወይም ስምሪት ሰጪው(ዋ) በሥራ ላይ ካልሆነ(ች)፣ የአውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) የአስቸኳይ አገግሎት እና የ MCPS DOT ሱፐርቫይዘር ወደ ቦታው መጠራታቸውን ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች።

b) አደጋ ወይም ግጭት ያጋጠመው አውቶቡስ ከፖሊስ ኦፊሰር ወይም ከ DOT ሱፐርቫዘር ፈቃድ ከመሰጠቱ/ከመለቀቁ በፊት ከቦታው መንቀሳቀስ የለበትም።

c) የፌደራል የትራንስፖርቴሽን ደረጃን በጠበቀ መልኩ፣ የአካል ጉዳት ያስከተለ ወይም ተሽከርካሪ በጎታች መኪና እስከሚጎተት የሚያደርስ ብልሽት አደጋ ሲያጋጥም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አሽከርካሪዎች የእፅ ሱሰኝነት ምርመራ ሲደረግ ትብብር ማሳየት አለበ(ባ)ት።

3. ማሳወቅ

a) አደጋዎች ለስምሪት ኃላፊ እና ለፖሊስ ወዲያውኑ/በአስቸኳይ ሪፖርት መደረግ አለባቸው።

b) የስምሪት ኃላፊው እንደአግባቡ ለሚመለከታቸው የ MCPS ባልደረቦች፣ አግባብነት ሲኖረዉ ለዋናው የሥራ ኃላፊ/Office of the Chief Operating Officer (OCOO) ጨምሮ፣ የማሳወቅ ቅደምተከልን በመከተል ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

c) የ DOT ባልደረባ ለ OCOO ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

d) ተማሪዎችን የሚያካትት አደጋ መከሰቱ እንደተሰማ፣ ርእሰመምህር-ት/ተወካይ በተቻለ ፍጥነት ለወላጆች/ለሞግዚቶች መግለጽ አለበ(ባ)ት።

e) በአደጋው ወቅት ተማሪዎች ወይም ሠራተኛ ጉዳት ደርሶባቸው ሆስፒታል ገብተው ከሆነ፣ የአስተዳደር ወይም የቁጥጥር ባልደረቦች ከትምህርት ቤት እና ከ DOT ወደ ሆስፒታሉ ይላካሉ።

f) የመረጃ ጥያቄዎችን በሚመለከት የኮሙኒኬሽን ዲፖርትመት የዜና መረጃዎችን በሙሉ ያስተናግዳል።

4. ሪፖርት ስለማድረግ

a) ስለሁሉም አደጋዎች የሪፖርት አቀራረብን እና የምርመራ ሂደቶችን በመከተል DOT ያከናውናል።

b) DOT የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንትን የአደጋ ሪፖርት አቀራረብ መመሪያዎችን በሙሉ ተግባራዊ ያደርጋል።

F. የመጓጓዣ መስመር ለውጥን ስለማሳወቅ

1. የ DOT ዳይሬክተር የአውቶቡስ አገልግሎትን በሚመለከት ማንኛውም ትልቅ ለውጥ ከተደረገ አዲሱ የትምህርት ዓመት ከመጀመሩ በፊት በጁን ወር ወይም በዓመቱ ውስጥ የተደረጉትን ትልቅ ለውጦች ከአስር ቀን በፊት ለርእሰመምህር ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

2. የአውቶቡስ ማቆሚያዎች በ DOT ዳይሬክተር/ተወካይ አማካይነት ለውጥ ሲደረግ፣ ርእሰመምህር ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ ስለተደረገው ለውጥ ወቅታዊ የሆነ መግለጫ ይሰጣል/ትሰጣለች። ርእሰመምህር(ት)፣ ከ DOT ዳይሬክተር/ተወካይ ጋር በመተባበር፣ ለሚመለከተው ወላጅ/ሞግዚት ደብዳቤ ረቂቅ ያዘጋጃል-ታዘጋጃለች። ከርእሰመምህር-ት ለወላጆች/ለሞግዚቶች የሚላከው ደብዳቤ፣ የሚከተሉትን ያካትታል–

a) በአገልግሎቱ ላይ የሚደረገው ለውጥ፣ ለሚወሰደው እርምጃ ምክንያቱን ጭምር

b) መጓጓዣው የሚቋረጥበት ቀን/ጊዜ

c) አዲሱ የአውቶቡስ መቆሚያ ቦታ፣ የሚሆን ከሆነ።

d) ስለ አዲስ የመተላለፊያ ጥበቃዎች ምደባ ወይም የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች ጋር የሚዛመዱ መረጃዎች፣ የሚሆን ከሆነ፣ እና

e) ስለተደረገው ለውጥ የይግባኝ አቀራረብ ስርአት።

G. ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጪ ለመስክ ጉዞዎች፣ ለአትሌቲክስ፣ እና ለሁነቶች የአውቶቡስ አጠቃቀም

1. ከመደበኛ የጉዞ መርኃግብር ጋር በማይጣረሱ ወይም ጣልቃ በማይገቡ ሠአቶች ለሚደረጉ የመስክ ጉዞዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አውቶቡሶች ይኖራሉ። ጥቂት አውቶቡሶች በመደበኛ የአውቶቡስ መስመር ላይ አይመደቡም እና በማንኛውም ሠዓት ለቀን ለጉዞ ወይም ለበርካታ ቀናት ጉዞዎች የተወሰነ ቁጥር ያላቸው አውቶቡሶች ይገኛሉ።

2. ትምህርት ቤቶች ለተፈቀደላቸው የኤክስትራከሪኩላር እንቅስቃሴዎች ተሳታፊዎችን ለማጓጓዝ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አውቶቡሶችን መጠቀም ይችላሉ።

3. የሞንትጎመሪ ካውንቲ፣ የሮክቪል ከተማ፣ የጌትስበርግ ከተማ፣ የታኮማ ፓርክ ከተማ፣ የመሣሰሉ የመንግስት ድርጅቶች እና/ወይም ከትምህርት ጋር የተገናኙ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች በ DOT ዳይሬክተር በተፈቀደው መሠረት፣ የ MCPS የትምህርታዊ ዓላማን ለማስፋት ለትምህርት ዓላማ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አውቶቡሶችን መጠቀም ይችላሉ።

4. ለትምህርት ቤት የመስክ ጉዞዎች እና ለሌሎች የማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ፕሮግራሞች አውቶቡሶችን ስለመጠቀም ዋና የሥራ ኃላፊ አልፎ አልፎ የከፍያ ሁኔታን ክለሣ በማድረግ ይወስናል/ትወስናለች። መርኃግብሩ የስራ ማስኬጃውን እና የአሽከርካሪ ወጪዎችን ይጨምራል። የ DOT ድረ-ገጽ ያመሣክሩ፣ WebTrips:Field Trip Request System፣ዝርዝሩን ለማወቅ።

5. DOT በማቴሪያል ማኔጅመንት ዲፓርትመንት ከእቃ ግዢ ክፍል ጋር በመተባበር ትምህርት ቤት ስፖንሰር ለሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ከዚህ የሚከተሉትን ደረጃዎች የሚያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የግል ተሽከርካሪዎችን የመመልመል ኃላፊነት አለበ(ባ)ት።

    a) ካምፓኒው አስፈላጊውን የመድን/የኢንሹራንስ ደረጃዎች ይሸፍናል።

    b) በፌደራል መስፈርት መሰረት ተሽከርካሪዎቹ በሙሉ ምርመራ እየተደረገባቸው ቁጥጥሩን ማለፍ አለባቸው።

    c) አሽከርካሪዎች ተገቢ የመንጃ ፈቃድ ይኖራቸዋል እና አስፈላጊ ስልጠናዎችን በሙሉ ያገኛሉ።

    d) አጓጓዡ(ዧ) በፌደራል መስፈርት መሠረት የእፅ መዳኒት ምርመራ/ቴስት እና ለሞተር አሽከርካሪነት ሥራ መስፈርቶችን ያሟላል/ታሟላለች።

6. ለተማሪዎች ኃላፊነት

    a) በ MCPS አውቶቡሶች በሚደረጉ ጉዞዎች የትምህርት ቤት ቡድን አባል የሆነ/ች ባልደረባ፣ በርእሰመምህርት/በተወካይ የተፈቀደለ(ላ)ት-የጉዞ አጃቢ አገልግሎት ላይ በሚዉል እያንዳንዱ አውቶቡስ ላይ አብሮ መሣፈር ግዴታ/mandatory ይሆናል። የአውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) የሥራ ባልደረባ ወይም የተፈቀደለ(ላ)ት አብሮ ተጓዥ በአውቶቡሱ ላይ ሳይሳፈሩ ጉዞ መጀመር አይፈቀድለ(ላ)ትም።

    b) ኃላፊነት ያለበ(ባ)ት የሥራ ባልደረባ ወይም የተፈቀደለ(ላ)ት የጉዞ አጃቢ ስለ ጉዞ ደህንነት እና ቁጥጥር በ MCPS Regulation IPD-RA የተደነገገውን ማክበር ይኖርበ(ባ)ታል። Travel-Study Programs, Field Trips, and Student Organization Trips

H. የህዝብ ስጋቶችን መፍታት

በቦርድ ፖሊሲ/Board Policy KLA ላይ በተደነገገው መሠረት፣ ከህዝብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ ስለመስጠት/Responding to Inquiries and Complaints from the Public፣በሁኔታው ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች በትብብር እና ስምምነት በማድረግ ማህበረሰቡ በማስማማት ሂደት መፍትሔ እንዲያገኝ ቦርዱ ያበረታታል። ይፋዊ የሆኑ እርምጃዎች በሞንትጎመሪ

ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/MCPS Regulation KLA-RA ላይ በተደነገገው መሠረት፣ ከህዝብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ ስለመስጠት/Responding to Inquiries and Complaints from the Public፣ ቅሬታዎችን ለመፍታት መጠቀም የሚያስፈልገው በጋራ ስምምነት ለመፍታት የሚደረገው ሙከራዎች ካልተሳኩ ብቻ ነው።

1. ስለተማሪ መጓጓዣን በሚመለከት ጥያቄ፣ ስጋት፣ ወይም ቅሬታ ያለው/ያላት የማህበረሰብ አባል ተገቢ ስምምነት ላይ ለመድረስ ከ DOT ክለስተር ሱፐርቫይዘር ጋር ውይይት እንዲያደርግ-እንድታደርግ ይበረታታል።

2. በ DOT ሱፐርቫይዘር ደረጃ በጋራ ስምምነት መፍትሔ ያልተገኘበት ጉዳይ ለውሳኔ ወደ DOT ዳይሬክተር ይተላለፋል።

3. የ DOT ዳሬክተር ውሳኔ ሱፐርኢንተንደንቱን በመወከል ውሳኔ መስጠት ለሚችለው አካል የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy KLA በሚደነግገው መሠረት እስከ ቦርድ ድረስ ይግባኝ ለማቅረብ እንደሚቻል በመግለጽ፣ ይግባኙ ለዋና የሥራ ኃላፊ ሊቀርብ ይችላል Responding to Inquiries and Complaints from the PublicMCPS Regulation KLA-RA፣ Responding to Inquiries and Complaints from the Publicand the Education ArticleThe Annotated Code of MarylandSection 3-903(c)።

**ተዛማጅ ምንጮች፦** Annotated Code of Maryland፣ Education Article፣ §3-903(c)፣ Code of Maryland Regulations §13A.06.07፣ Student Transportation፣ Individuals with Disabilities Education Improvement Act of 2004፣ as amended፣ Title I፣ Part A §602(26)(A)፣ McKinney-Vento Homeless Assistance Act of 1987፣ as amended፣ Title VII፣ Subtitle B፣ 42 U.S.C. 11432 (g)(3)as amended by the Every Student Succeeds Act of 2015፣ and Rehabilitation Act of 1973፣ as amended፣ 20 U.S.C. §794 (Section 504)።

የደንቡ ታሪክ፦ ቀደም ሲል Regulation No 215-1፣ ሴፕቴምበር 12/1979 የተሰኘ፣ directory information updated January, 1983; ዲሴምበር/1984 ተሻሽሏል፣ ኤፕሪል/1988 ተሻሽሏል፣ ሜይ 13/1998 ተሻሽሏል፣ ኤፕሪል 21/2010 ተሻሽሏል፣ ኦገስት 22/2019 ተሻሽሏል።